**ከደብተራው ድረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል ማስታወሻ፣**

ታላቁ የጥበብ ሰው ገሞራው በ1999 ዓ. ም "የቅዱሳንን ዐጽመ-ርስት ርኵሣን አይወስዱትም! (የማስጠንቀቂያ ጦማር!)" በሚል ርዕስ የፃፈውን በሁለት ተከታታይ ክፍሎች ልኮልን በድረ-ገፃችን ላይ አትመነው ነበር። "... የታላቅና ክቡር ውድ አባት ዐጽመ-ርስት የሆነውንና በይዞታው ንብረትነት ለዘመናት የቆየውን ቦታ ኢሕጋዊ በሆነ መንገድ በዘረፋ ወስደዋል። ... " በማለት ጀምሮ "... አሁን ይህን ቦታ በዳረጎትነት ተሰጠኝ ብሎ የሚጨፍረውና ጮቤ የሚረግጠው ሰው በቀጣዩ የፍትሕ ወቅት የደም እንባ ከሚያለቅስ ዛሬውኑ አስረክቦ ዞር ቢል ይመረጣል። ... " ብሎ ያጠቃለለውን ጽሑፍ የደመደመበትን ግጥም (ቀጥሎ በቀይ ቀለም የተቀመጠው) ያልሆነ ትርጉም እየሰጡ፣ ጥቂት ሰዎች የዚህን ክቡር የኢትዮጵያ ልጅ አስከሬን ከወያኔ ጋር ለመሞዳሞድ ሲያውሉት ታዝበናል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ በ እኛ በኩል በሰፊው እንመለሥበታለን። ለዛሬው የቅርብ ወዳጃቸው አቶ ዘነበ በቀለ የላኩልንን ጽሑፍ ከዚህ በታች አቅርበናል።

# ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ ሀይሉ ገ/ ዮሐንስ/ ገሞራው" በሚል ርዕስ ከአቶ ጥበቡ በለጠ ሰንደቅ የቀረበውን ፅሁፍ በተመለከተ የቀረበ አስተያየት!

ከዘነበ በቀለ

ፅሁፉን እንደተረዳሁት ግላዊ አስተያየት እንጂ! የሀይሉን አስተሳሰብም ሆነ ማንነት ገላጭ ነው ብዬ አላምንም። አለመሆኑንም የሚከተለው ሁናቴ ያስረዳል።

ፀሀፊው እንዲህ ይላሉ: " አርባ ዓመታት በስደት የተንከራተተው ይህ ብርቅዬ ባለቅኔአችን ሀገሩ ኢትዮጵያን እጅግ የሚወድ ሰው ነበር ይላሉ። ሲሞት ግን መቀበሪያው ይህችን ከዓይነ ህሊናው የማትጠፋው ኢትዮጵያ እንደሆነች ግጥም ፅፏል። መቀበሪያዬ ኢትዮጵያ ናት እያለ።" ይሉና ግጥሙን እንደ ኑዛዜው በማስመሰል ያቀርባሉ። በመሰረቱ ኑዛዜ በአውሮጳ ውስጥ በጠበቃ ፊት ወይም በመንግስት ተቋማት ፊት ቀርቦ የሚደረግ የግለሰብ ሰነድ ነው። በሀገራችንም ቢሆን በተመሳሳይ ሁኔታ በንስሀ አባት ፊት በሀገር ሽማግሌዎች ፊት ወይም በመንግስት ተቋማት ውስጥ የሚከናወን ይሆናል። ከዚህ ውጭ በህይወት ዘመኑ በግል የፃፋቸውን ስነ ፅሁፎች ጠቅሶ ኑዛዜ ነው ማለት አይቻልም። ከዕልፈቱ በሁዋላ ቤቱ ውስጥ የመግባት መብት የተሰጣቸው ጥቂት ሰዎች አገኘን የሚሉት ፅሁፍ ካለ ሊያሳዩን ይገባል። አለበለዚያ ግን ጉንጭ አልፋ ተረብ ነው የሚሆነው።

ገሞራው ይህ ኑዛዜ ነው በተባለው ግጥም ላይ እንዲህ ይላል!

> ባያውቁት ነው እንጂ የኔን ቋሚ ትንግርት፣
> (እነማን ናቸው ያላወቁት? ዓላማውን ሊያስቱ የታገሉት ሁሉ ናቸው።)
> በተወለድኩበት ነው የምቀበርበት፣
> ሌላ ቦታ ሳይሆን በትውልዴ መሬት።
> (ኢትዮጵያ አፅመ ርስቴ ናት፣ ማንም ሊነቀንቀኝ አይችልም ለማለት ነው።)
> አስቀድሞም ቢሆን እትብቴ ተቀብሯል፣
> ቀሪው አካሌ በርግጥ በክብር ያርፋል።
> (እዚህ ላይ ነው ትልቁ መልዕክት ያለው)

በማን ስር ነው? ቀሪው አካላቱ በክብር የሚያርፈው? ሲታገለው በኖረው ሀይል ህዝቤን ነፃነት ገፎታል ብሎ ባለው ስርዐት ውስጥ ነው? በክብር የሚያርፈው? ፀሀፊው እንዳሉት ባለመሆኑም በስቶክሆልምም ሆነ በሀገር ቤት የቀብር ስነ ስርአቱ ለዘመናት ከተሰቃየለት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ውጭ የተከናወነ ነው።

ስነ ፅሁፍ በተለይም  የሀይሉ ፅሁፎች እንደወረደ የሚተረጉሟቸው አይደሉም። ገሞራው እንኳንስ ስነ ግጥሞቹ በማህበራዊ ውይይት ላይ አባባሉ የሚከብድባቸው ብዙ ሰዎች አሉ። በዚህ የግጥም ትሩፋቱ ሊያሳይ የሞከረው ፍላጎቱን ነው። ፍላጎቱ ደግሞ ነፃነት ነው። "ጎጆይም ጠላችኝ " በሚለው ግጥሙ ውስጥ እንዲህ ብሏል -

ለኔ መኖሪያ ያህል ከሰፊው ዩኒቨርስ፣
የማጣ አይመስለኝም ዓለሙን ባዳርስ።
..... ለሚቀረኝ ህይወት፣
ትነፍገኝ ይሆን ወይ ሩህሩሁዋ መሬት?

ሲል የሚማፀነው፣ የሀገሩን መሪር ሀዘን ለመግለፅ ነው። ያ! ማለት ግን ከሀገሬ ወጥቼ እቀራለሁ ማለቱ አይደለም። ሀገሬን ጠላሁዋት ማለቱም አይደለም። ሁሉም አባባሉ ተስፋውን የሚጠቁም ነው። ብስጭቱን የሚገልፅ ነው። ምኞቱ "በሀገሬ ኢትዮጵያ አካሌ በክብር ያርፋል።" በሚለው ሀረግ ውስጥ ይጠቃለላል። ሀይሉ ምኞቱ ሁሉ ስለተሟላለት ሀገሩ ገብቶ ማረፍን መርጧል ብሎ ማለት ግን ወያኔያዊ አመለካከት ነው። ይህን ሊያስብል የሚያስችል አንድም ሀቅ የለም። የታገለለት ህዝብ ነፃነት ከመቼውም በላይ እየተረገጠ ነው። ሀገሩ በባዕዳን ኢንቬስተሮች መዳፍ ስር ውላለች። መሬቱ በሊዝ ተቸብችቦ አልቋል። ህዝቡ እየተፈናቀለ መኖሪያ አጥቷል። ታዲያ ገሞራው ነው በዚህ ሁኔታ ሀገሬ ቅበሩኝ አለ የሚባልለት? እንኳንስ ለሚያውቀው ፅሁፉንም በውል ለተረዳ የማይመስል ቅጥፈት ነው የሚሆነው። የሀይሉ ገሞራውን አስከሬን ለወያኔ እጅ መንሻ ለማድረግ የተረባረቡ ሀይሎች ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ ታይቷል። ለዘመናት የደከመባቸውን ስራዎቹን ከቤቱ አውጥቶ ለወያኔ ማስረከብ እንደሆነ ተስተውሏል።

ሌላው የተሳሳተ መልዕክት እንዲህ ይነበባል -  ”በ 1928 ዓ.ም. በልጅነት ግዕዝና የቤተ ክህነት ትምህርትን ጠንቅቆ የተማረና ............ በዚህም የተነሳ የግዕዝን ቋንቋ የሚቀኝበት፣ የሚፅፍበት፣ የሚናገርበትም አድርጎት ነበር።” ይላል ፅሁፉ፣ በመሰረቱ ሀይሉ 1928 ሳይሆን በ1935 ነው የተወለደው በሌሎች ፅሁፎች ላይ እንደሰፈረው። ሳይወለድ ቅኔ መቀኘት አይችልም። ቁጥሩ ተሳስቶ ነው በ38 ማለቴ ነው ቢባል እንኳ አባባሉ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም በኦርቶዶክስ ሀይማኖት እምነት ልጅ ትምህርት መጀመር አለበት የሚባለው በአራት ዓመት ከአራት ቀን እንጂ በሶስት ዓመቱ አይደለም። እንኳንስ ከቤተክህነት ምሁር ቤት የተገኘው ቀርቶ በሌሎቻችንም በተግባር የሚውል ነው። ሀቅን አንሸዋሮ ማቅረብ ለምን አስፈለገ?

ገሞራው፣ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ተከታትሎአል። ቅድስት ስላሴ መንፈሳዊ ት. ቤት በተማሪነት፣ ዳግማዊ ምኒልክ ት.ቤት በተማሪነት፣ ሀረር ምምህራን ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በተማሪነት፣ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ በተማሪነት፣ ተግባረዕድ ት. ቤት በመምህርነት፣ ደብረብርሃን መምህራን ማሰልጠኛ በመምህርነት፣ ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ በመምህርነት በመጨረሻም እቴጌ መነን ትምህርት ቤት በመምህርነት ሲያገለግል ወደ ቻይና ለከፍተኛ ትምህርት ሄዷል። በእያንዳንዱ ስፍራ የቅኔ ዝማ ፈሶባቸዋል። ከማውቀው ውስጥ በኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ውስጥ ሳለ "ጎጆዬም ጠላችኝ የሚለውን፣ በዩኒቨርስቲ ውስጥ ሳለ በረከተ መርገምን፣ በእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ውስጥ ሳለ "በናቴ እኮ ሴት ነኝ" የሚለውን ድርሰቱንና ሌሎችንም በርካታ ስራዎች አበርክቷል። በቻይናም ሀገር ሳለ

A Tiny Home of Chinese – English Idiomatic Phrases : ” To cut ones feet, Just for the shoes to feet” compiled by Hailu

በኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ውስጥ በመምህርነት ስናገለግል በርካታ መዝሙሮችንና ግጥሞችን አብረን ሆነን እናቀናብር ነበር። መምህር ፀጋሰው ወልደ አረጋይ ባዘጋጀው የመምህራን መዝሙር ላይ

"የገበሬው አባት – የዶክተሩ አባት፣
የመሃንዲሱ አባት – የወታደሩ አባት፣
መምህር አንተ ባትኖር መካን ነበር ህይወት"

የሚለውን አዝማች የጨመረው ሀይሉ ነበር። ከዚህ ጊዜ በሁዋላ በሞት እስከተለያየንበት ጊዜ ድረስ ከአርባ አምስት አመታት ያላነሰ አብረን ነበርን። ምናልባት ከኔ የበለጠ በሞቱ የተጎዳ ሰው ይኖራል ብዬ አላምንም። የአሁኑም አገሬ ቅበሩኝ አለ የሚለው አባባል ለኔ ቧልት መስሎ የታየኝ ለዚያ ነው። ያተረጓጎም ስህተት አለ ብዬ አላስብም ይልቁንስ የተቀናበረ ደባ ነው የሚመስለኝ፣ ከአንድ ዓመት በፊት ነው "በመንጎሌ ጥሪ" ብዕር ንቀል ያለው ሀይሉ። እና ከየት የመጣ ነው አንድ አመት የማይሞላው በግጥም ልተንፍስ የሚለው ግጥሙ?ለምሳሌ በበረከተ መርገም ውስጥ

" አንቺ ያገሬ ዝንብ የሰይጣን ንቢቱ፣
ከጥንት ጀምሮ አዳሜ ሲሰድብሽ ያላግባብ በከንቱ፣
ሙያሽን ሳያውቀው ያላንዳች ምክንያት እንዲያ ሲጠየፍሽ
በደነዝ ስሜቱ፣
አንቺ ግን በውነት ለውነት ስትዪ ሀሞትሽን ኮስትረሽ ስለኖርሽ በድካም፣
የሀገር ጭነትን የብሄር ሸክምን የወገን አላልን፣
አርጋጂን አንጓጂን ለማጥፋት ለማውደም፣
ጠንቃዊ ነፍሳቱን ጀርሙን ትላትሉን ከዳሪ ወደቤት ስታመላልሺ
ለፈፀምሽው ጀብዱ፣
አምላክ ተመልክቶ በኪነጥበቡ ሳምሶንን ያድርግሽ በለጋስ ልማዱ።

በማለት ስለመረቃት ደራሲው ዝንብ የሚወድ ስለሆነ ነው እሷን ብቻ ለይቶ ያመሰገናት ብሎ የሚፈርጅ አንባቢ ካለ ግንዛቤውን ከግምት ውስጥ ከማስገባት ውጭ አስተያየቱ ፋይዳ ይኖረዋል ብዬ አልገምትም። ጎዳናው አይደለምና።

የገሞራው ግጥሞች ተምኔታዊ ናቸው። በዚያ አኳያ ነው መመልከት የሚቻለው። ከዚህ በተረፈ ገሞራው በርካታ የሰበሰባቸው ዶኩሜንቶች ምርምር ያካሄደባቸው ፅሁፎች መወሰዳቸው የማይቆረቁረው ኢትዮጵያዊ አለ ብዬ አላምንም። ለዚህ አይነቱ ዝርፊያ ምክንያት የሆኑ ሰዎች ደግሞ ምንም ጊዜ ቢሆን በታሪክ ተጠያቂ ናቸው።

በገሞራው አባባል ፅሁፌን ልደምድም።

ደህና መሆንን እናርግ!!